

# በጌትሰማኒ የአትክልት ሥፍራ ኢየሱስ ያደረገው ፀሎት

የፋሲካን እራት አብረው ከበሉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የሆነው የአስቆሮቱ ይሁዳ ኢየሱስን ለካህናትና ለገዢዎች አሳልፎ ሰጠው። እነኝህ ሰዎች ኢየሱስን ለማሰር አጋጣሚ ሲጠብቁ የነበሩ ሰዎች ናቸው። ኢየሱስ ይህ እንደሚሆን አስቀድሞ ያውቅ ነበር። አስቀድሞም ለደቀ መዛሙርቱ ከመካከላቸው አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠው ነግሯቸው ነበር።

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ትቷቸው እንደሚሄድ፣ እንደሚሞትና ነገር ግን እንደገና ከአባቱ ጋር እንደሚኖር ነገራቸው። እንዲሁም አባቱ ረዳት እንደሚልክላቸው ነገራቸው። ይህም ረዳት መንፈስ ቅዱስ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ የሚለውን መረዳት አልቻሉም/

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ እራት አብረው ከበሉበት ክፍል ከወጡ በኋላ በቀጥታ የሄዱት ወደጌትሰማኒ የአትክልት ስፍራ ነበር።

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን በአንድ ስፍራ እንዲጠብቁት ከነገራቸው በኋላ ወደአባቱ ለመፀለይ ትንሽ ራቅ ብሎ ሄደ። ከጥቂት ቆይታም በኋላ ኢየሱስ ወደደቀመዛሙርቱ ተመልሶ መጣና ተኝተው አገኛቸው። በጣም አዝኖ ነበር። እንደገና ሊፀልይ ሄደ። ሶስት ጊዜ እንዲሁ አደረገ። ሆኖም ደቀ መዛሙርቱ ደክሞአቸው እንቅልፍ ተጫጭኗቸው ነበር።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ከእንቅልፋቸው ቀስቅሷቸው እያነጋገራቸው እያለ ይሁዳ መጣ። ይሁዳም ኢየሱስን አየውና ቀደም ብሎ ሄዶ ሳመው። ይህም ለተከተሉት ወታደሮች ኢየሱስ ማን እንደሆነ የሚለዩበት ምልክት ነበር። በዚያ የነበሩት ወታደሮችም ኢየሱስን መጥተው ያዙት። ጴጥሮስ መዋጋት ፈልጎ ነበር። ኢየሱስ ግን ከለከለው።

ኢየሱስ ከያዙት ሰዎች ጋር ለመሄድ ተስማማ።

*ይህ ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 26፡ 36 – 45 እና በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 22፡ 39- 52 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com